

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከፌብርዋሪ 11-20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

## እንዲሁም

## ከፌብርዋሪ 21-28/2026 እና ከማርች 1-10/2026 የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ፌብርዋሪ 2026

አዲስ አበባ


ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

### 1. እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ


በፌብርዋሪ የሁለተኛዉ አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች በስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች ላይ የተሸላ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በጥቂት የደቡብ ምዕራብ እና በስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች፣ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ5 ሚ.ሜ በላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ5 ሚ.ሜ በላይ ቀላል መጠን ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አማን 8.9፣ ቦሬ 8.3፣ ቡሬ 8.5፣ ቡረጂ 17.8፣ ጭራ 10፣ ጋቲራ 13.3፣ 8.4፣ 14.6፣ 7.4፣ 9.2፣ እምድብር 12.6፣ ጅንካ 16.1፣ 10.9፣ ማጂ 24.3፣ ማሻ 10፣ ሰዉላ 9.3፣ 12፣ ቴፒ 11.3፣ 5.7፣ ቡልቂ 10.6፣ 25.6፣ 10.4፣ እንዲሁም ዲመካ 7.4 ሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በአስር (10) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ10 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡





ምስል1:ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ10 ሚ.ሜ በላይ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ በደቡብ ምዕራብ፣ በጥቂት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል እን የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች ላይ ከ3-57 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-8 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ቡኖ በደሌ፣ ኢሊባቦር፣ ጅማ፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጥቂት የቦረና ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ኮንታ፣ ምዕራብ ኦሞ እና የከፋ ዞኖች ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፤ ጋምቤላ፣ በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ35.0-44.6 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 2) ።


Ethiopian Meteorology Institute




ምስል፡2 ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ35 ዲ.ሴ በላይ የተመዘገበባቸው

## 1.2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው የፌብሪዋሪ ሁለተኛ አስር ቀናት የደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ የሃገሪቱ ክፍሎች ላይ መጠነኛ የአፈር ውስጥ እርጥበት እንደነበራቸው የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም ሁኔታ በተለይም የበልግ አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግ፣ ለቋሚ ተክሎችተክሎች የውሃ ፍላጎትን ለማሟላት፣ ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለማሻሻል ጠቀሜታ የነበረው ሲሆን፤ በተለይም የበልግ አብቃይ በሆኑት በደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች የነበረው የአፈር ውስጥ እርጥበት የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና የተለያዩ የበልግ ወቅት ሰብሎችን አስቀድሞ ለመዝራት ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4)።





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

### 1.3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አሥር ቀናት በአብዛኛው ዋቢ ሸበሌ፣ የአባይ፣ የተከዜ፣ የአዋሽ፣ የስምጥ ሸለቆ፣ የአይሻ፣ የመረብ ጋሽ እና የኦጋዴን ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር የነበሩ ሲሆን ሆኖም በጥቂት የመካከለኛውና የታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ የመካከለኛው አባይ እንዲሁም በጥቂት ታችኛው ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የገጸ ምድር ውሃ ፍሰት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህ ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ለውሃ ሀብት አቅርቦት መጠነኛ አስተዋፅዖ ነበረው (ካርታ 5)።

Ethiopian Meteorology Institute




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## 2. መግቢያ

የፌብርዋሪ ወር በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ የሚጀምርበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የደቡብ ምዕራብ፣ ደቡብ፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የመካከለኛውና አጎራባች የስምጥ ሸለቆ ሥፍራዎች የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት ስምንት ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ መደበኛ ቦታዎቻቸውን የሚይዙበትና የሚጠናከሩበት ጊዜ በመሆኑ በተለይም በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋንና የእርጥበት መጨመር ይኖራል፡፡


### 2.1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21-28/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በፌብርዋሪ የሶስተኛው ስምንት ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች፣ መካከለኛውና ደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን ይጨምራል፡፡ በተለይም በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ በመካከለኛው፣ የስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ በሌላ በኩል በጋምቤላ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅና በደቡብ ምስራቅ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ32-39.9 ዲግሪ ሴልሺየስ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)።


Ethiopian Meteorology Institute




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 21-28/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 21-28/2026 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ምስል 3፡ ከፌብርዋሪ 21-28 በ24 ሰዓት ውስጥ ከሰላሳ አምስተ (35) ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ የሚመዘገብባቸዉ ስፍራዎች

## ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን |
| አሮሚያ | ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን እና የምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ | ቀላል መጠን (ከ10 ሚ.ሜ በታች) |
| ሶማሌ | ዳዋ እና ሊበን ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ10 ሚ.ሜ በታች) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ጋሞ፣ የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ10 ሚ.ሜ በታች) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ10 ሚ.ሜ በታች) |

| በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | |
|---|---|---|
| አሮሚያ | ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን እና የምዕራብ የሸዋ፣ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ | ቀላል መጠን (ከ10 ሚ.ሜ በታች) |
| አማራ | የሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ10 ሚ.ሜ በታች) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | በጥቂት የጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ቀላል መጠን (ከ10 ሚ.ሜ በታች) |
| አዲስ አበባ፣ | | ቀላል መጠን (ከ10 ሚ.ሜ በታች) |

## 2.2 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በማርች የመጀመሪያው አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከዕለት ወደ ዕለት አንፃራዊ መጠናከር እያሳዩ በመሄድ የወቅቱ ዝናብ በበልግ አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋና እየተጠናከረ ይመጣል፡፡ በመሆኑም በተለይም በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋንና የዝናብ ስርጭት ይኖራቸዋል፡፡

በመጪዎቹ የማርች አሥር ቀናት አሁን እየተስተዋለ ያለዉ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖረዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ፣ መካከለኛው፣ ሰሜን ምስራቅ እና የስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

## 2.3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የፌብርዋሪ ሦስተኛው ስምንት ቀናት የሚኖረው እርጥበት የበልግ እርሻ እንቅስቃሴን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች በስፋት የማሳ ዝግጅት እና የዘር መዝራት ተግባራትን ለማከናወን ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በሚቀጥሉት ስምንት ቀናት የበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ አንጻራዊ በሆነ መልኩ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖር ይጠበቃል። ይህም ሁኔታ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፣ በመካከለኛው ዝቅተኛ አካባቢዎች ላይ የበልግ ወቅት የማሳ ዝግጅትን ለሚያከናውኑ አካባቢዎች የአፈርን እርጥበት ከማሻሻል በተጨማሪም ዘር ለመዝራት በጎ ሚና ሊኖረው እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ በሌላ በኩል በተቀሩት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ ሥፍራዎች ላይ ደረቃማ ቀናት እያመዘኑ ሊቆይ እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በሚቀጥሉት ቀናት የሚጠበቀዉን የእርጥበት ሁኔታና መልካም አጋጣሚዎች በተገቢው ሁኔታ ለመጠቀም እና አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ ከታች የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በአግባቡ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| የበልግ የግብርና እንቅስቃሴን ቀድመው የሚጀምሩ አካባቢዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
| ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን እና የምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ዳዋ እና ሊበን ዞኖች ጋሞ፣ የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ሲዳማ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ በጥቂት የጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | • አነስተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የሚኖረዉ የአፈር ውስጥ እርጥበት ለበልግ እርሻ ስራ በወቅቱ ለመጀመርና የማሳ ዝግጅት ለማካሄድ<br>• ለቋሚ ተክሎች ዕድገት<br>• የግጦሽ ሳር እና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለማሻሻል | • ለሰብል መዝራት በቂ ያልሆነ እርጥበት መኖር<br>• ደረቅ ሰሞናት መኖር<br>• የትነት መጠን መጨመር | • የበልግ እርሻ እንቅስቃሴ ቀድመው የሚጀምሩ አካባቢዎች የሚገኘውን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም የማሳ ዝግጅት ማካሄድ |

### 2.4 እ.አ.አ ከፌብርዋሪ 21-28/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀትሉት ፌብርዋሪ ስምንት ቀናት በተወሰኑ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፈስት ያገኛሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት በሰንጠረዥ የተቀመጠው በተፋሰስ ተኮር የቀረቡትን የውሀ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦችን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውሀ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| • በላይኛው አዋሽ፣ በላይኛው እና በመካከለኛ ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት በላይኛው ገናሌ ዳዋ | • ከመካከለኛ እስከ ከመጠነኛ | • <br>• ከዕለት ወደ ዕለት የገጸ ምድር ወሀ እየተሻሻለ መሄድ | • እንጻራዊ የትነት መጨመር<br>• በዉሃ አካላት አቅርቦት ጫና መኖር | • ውሃን በተገቢ ሁኔታ በማሰባሰብ<br>• የሚገኘውን መጠነኛ የሆነ የዝናብ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት መጠበቅ |
| • በአብዛኛው፣ ተከዜ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ አዋሽ፣ ገናሌ ዳዋ፣ አፋር ደናክል፣ መረብጋሽ፣ ኦጋዴን እና አይሻ፣ | • ደረቅ ሁኔታ | • ወንዞች እና ሌሎች የውሃ አካለት በደራሽ ቆሻሻ አለመበከል | • የወንዞች እንዲሁም በሌሎች የዉሃ አካላት መጠን መቀነስ | • ዉሃን በአግባቡ መጠቀም<br>• የውሃ መቆጠብያ ዘዴዎች መተግበር |